


## ማብራሪያ

አንድን ሙስሊም ከኢስላም ሊያወጡት የሚችሉ፣ ኩፍርን እንጂ ምንንም የማያሳዩ ንግግሮችና ተግባራት ሳይገኙበት፣ ዲን ውስጥ ቁርጥ ተደርገው መታወቅና መተግበር ያለባቸውን ለምሳሌ የሰላትን ግዴታነት ውድቅ እስካላደረገ ድረስ፣ የአራጣን እርምነት፣ በኢስላምና ቁርአን አለመገዛትና በነርሱም ላይ ማሾፍ፣ ሸሪዓ ጊዜው ያለፈበትና ለዚህ ዘመን የማይጠቅም ነው እስካላለ ድረስ በአንዲት ነገር ማክፈር እጅግ አደገኛ ነው።

ነገርግን የኢስላማዊውን ዓቂዳ ሳይክድ ከማፅደቁ ጋር ወንጀል ላይ ቢወድቅና ቢሰራ፣ ከአንድ በላይ ትርጉም አዘል ውስጠ ወይራ ንግግሮችን ስለተናገረም አናከፍረውም።

እዚህ ጋር ግን ሳንጠቅስ የማናልፈው አንዳንድ ተግባራት እና ‹መተዎች› በሸሪዓ እንደመጣው ኩፍር የሚለውን ቃል መጠቀም እንዳለብን ነው። ለምሳሌ ፡- ‹‹ሰላትን መተው ኩፍር ነው››። ነገርግን አንድ ሰው ነጥሎ ካፊር ለማለት ከምላሱ በርግጠኝነት የሰላትን ግዴታነት የሚያስተባብልበትን መረጃ ማግኘት ግዴታ ነው።

ሌላው ማወቅ ያለብን ቁምነገር ኩፍር ሁለት ዓይነት መሆኑ ነው። ባልደረባውን ከኢስላም ክልል የማያስወጣው ትንሹ ሺርክ ሲሆን፣ ትልቁ ደግሞ ከኢስላም ያስወጣዋል። በዚህ ልዩነት ብርሃን በመታገዝ ለምሳሌ ፡- ‹‹ከአላህ ውጪ ባለ አካል የማለ ሰው አጋርቷል›› የሚለውን። ይህ ከኢስላም የማያስወጣ ነገርግን የከበደ ወንጀል ነው።

ይህን 20 መርህ አስጀምሮ ላስጨረሰን አላህ በመጀመሪያም በመጨረሻ ምስጋና ለርሱ ነው።

***ተጠናቀቀ***

***1441***